DISRUPTING HARM

# በኢትዮጵያ ያሉ ሕፃናትን ከበይነ-መረብ ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል መከላከል - ቀጣዩ ሂደት

**በኢትዮጵያ ያሉ ሕፃናት የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ስጋት ያንዣበባቸው እና አደጋውም የምር እየደረሰባቸው ይገኛል። በዲስረፕቲንግ ሀርም ጥናት የተሰበሰበው እጅግ የቅርቡ ጊዜ ጥሬ መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ከአሥሩ የበይነ-መረብ ተጠቃሚ ሕፃናት መካከል አንዳቸው የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ተጎጂዎች ሆነዋል። በምልእተ-ሕዝቡ ዘንድ ስለ በይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ያለው ግንዛቤ እና ዕውቀት ውሱን ነው፤ የመከላከል እንቅስቃሴዎች ገና አልዳበሩም፤ ተጎጂዎችም የሚያገኙት ድጋፍ አናሳ ነው። ለበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምላሽ ለመስጠት እና በኢትዮጵያ ባሉ ሕፃናት ላይ አሁን እያደረሰ ያለውን እና ወደፊትም እያስከተለ የሚቀጥለውን ጉዳት ለመግታት፤ መንግሥት፣ ሕዝባዊ ተቋማት፣ እና ኅብረተሰቡ የተሻለ እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላሉ።**

## ምክረ-ሐሳቦች

የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የሚያደርሰውን ጉዳት መግታት እና ለተጎጂዎች የተሻለ ድጋፍ መስጠት፤ መንግሥታዊ ኃላፊነት-የተጣለባቸውን፣ የሕግ አስከባሪ መሥሪያ ቤቶችን፣ የፍትሕ እና የማኅበራዊ ድጋፍ አገልግሎት ባለሙያዎችን፣ የቴክኖሎጂ ኢንደስትሪውን፣ እና የማኅበረሰቡን ሁለንተናዊ እና ያላሰለሰ ጥረትን ይጠይቃል። ዲስረፕቲንግ ሀርም በኢትዮጵያ ፤ ለበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሁለንተናዊ እና ያላሰለሰ ምላሽ አሠጣጥን እውን ለማድረግ እንደሚያግዝ ተተግባሪ ወይም መሪ ዕቅድ ሆኖ ሊታይ የሚችል ሰነድ ሲሆን፤ ይህም የሕግ ማእቀፍን፣ የሕግ ማስከበርን፣ የሕግ ሂደቶችን፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን፣ እና የኅብረተሰብ ግንዛቤን ባጠቀሱ በማስረጃ በተደገፉ ምክረ-ሐሳቦች ታግዞ የቀረበ ነው። እነዚህ ምክረ-ሐሳቦች የኢትዮጵያ መንግሥት እና አጋሮቹ እርምጃ እንዲወስዱ፣ በገንዘብ እንዲደግፉ፣ እና እንዲያስተምሩ ጥሪ የሚያደርግ ይዘት ያላቸው ናቸው።

### እርምጃ

- በበይነ-መረብ ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ ትንኮሳ (sexual harassment)ን፣ የሕፃናት ወሲባዊ በደልን በቀጥታ-ሥርጭት ማስተላለፍን፣ እና ለወሲብ አስገድዶ-መጠቀም (sexual extortion)ን በማያሻማ መልኩ በወንጀል ድርጊትነት እንዲደነገጉ የሚያስችል የሕግ ማሻሻያ ማድረግ፤
- ለወሲብ ዓላማ በበይነ-መረብ የሚፈጸም የማሽኮርመም (grooming) ወንጀል ላይ ያሉ ሁኔታዎችን በሚያካትት መልኩ የሕግ ማሻሻያ ማድረግ፤ ሁኔታዎቹም ወሲባዊ በደሉ የደረሰው ወይም የተፈጸመው የአካል ግንኙነት በመደረጉ ሳይሆን በበይነ-መረብ አማካኝነት የሚፈጸሙበት ሁኔታዎችን ጨምር ማለት ነው። ለምሳሌ ሕፃናትን በማታለል ወሲባዊ በደል አዘል ቁሳቁሶችን/ይዘቶችን (Child Sexual Abuse Aaterial (CSAM)) አዘጋጅተው ለወንጀለኛው እንዲልኩ የሚደረግበትን ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል።
- ለሕፃናት-ምቹ የሆኑ እና የበይነ-መረብ አማራጮችን ጨምሮ፤ ሕፃናት የሚያሳስቧቸውን ጉዳዮች ለማሳወቅ፣ በገጠሟቸው ክሥተቶች ላይ አቤቱታ ለማቅረብ፣ እንዲሁም ዕርዳታ እና ምክር ለመጠየቅ የሚያስችሏቸውን አሠራሮች ማጠናከር እና ማብዛት፤
- የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮችን (case) ለፖሊስ ማመልከት የሚቻልባቸውን ግልጽ የአቤቱታ ማቅረቢያ ሂደቶችን መዘርጋት፤ እንዲሁም ለሕፃናት-ምቹ የሆነ አሠራርን ለመተግበር እንዲቻል ለሁሉም የፖሊስ አባላት ሰፊ ሥልጠና የተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ፤
- በወንጀል የፍትሕ ሂደት ወቅት ለሕፃናት ቃለ-መጠይቅ/ቃል መቀበል ስለሚደረግበት አግባብ የሚደነግግ መመሪያን ማዘጋጀት እና መተግበር፤ እንዲሁም ስለ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮች አያያዝ እና ለሕፃናት-ምቹ ስለሆነ ፍትሕ አሰጣጥ ላይ ያተኮረ ሥልጠናን ለዐቃቤ-ሕጎች እና ለዳኞች መስጠት፤
- የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን የሚመለከት አቤቱታ ለሚያቀርቡ ሕፃናት (እና ለተንከባካቢዎቻቸው)፤ ካሣ የማግኘት መብታቸውን እና መከተል ስላለባቸው ሂደቶች ጨምሮ ስለ መብቶቻቸው የሚያብራራ መደበኛ ይዘት ያለው የመረጃ ጥራዝ እንዲሰጣቸው ማድረግ፤
- ማስረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያስችሉ ሚሥጥራዊ የመረጃ መለዋወጫ ፕላትፎርሞችን ጨምሮ፤ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና በሕግ አስከባሪ አካላት መካከል በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ዙሪያ መተባበር የሚያስችሉ አሠራሮችን መፍጠር፤
- ዘርፈ-ብዙ የበይነ-መረብ ወንጀሎች ላይ ክትትል የሚያደርገው የሳይበር ወንጀሎች የሥራ ክፍል፤ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነክ ነገረ-ጉዳዮችን የመለየት እና ለዓለም-አቀፍ የቴክኖሎጂ ፕላትፎርሞች የመምራት/የማስተላለፍ አቅሙን ማሻሻል፤ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምስሎች ሃገር አቀፍ የመረጃ ቋት እንዲቋቋም ማድረግ እና ከኢንተርፖል የ‹ዓለም-አቀፍ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ› (International Child Sexual Exploitation (ICSE)) የመረጃ ቋት ጋር ማስተሳሰር። የ‹ዓለም-አቀፍ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ› (ICSE) የመረጃ ቋት ለመመረጅ (intelligence) እና ምርመራ ለማካሄድ የሚያግዝ ሲሆን፤ ይህም ልዩ/ዓይነተኛ መርማሪዎች የሕፃናት ወሲባዊ በደል ነገረ-ጉዳዮችን የሚመለከቱ መረጃዎችን እንዲለዋወጡ ያስችላቸዋል።

Funded by End Violence Against Children

Implemented by ecpat INTERPOL unicef Office of Research-Innocenti

DISRUPTING HARM

- የሕፃናት ወሲባዊ በደልን የሚያሳዩ ቁሳቁሶች ተደራሽ እንዳይሆኑ በማድረግ፣ ክሥተቶችን ተከታትሎ በማወቅ እና ሪፖርት በማድረግ፣ እንዲሁም የሕግ አስከባሪ አካላት ለሚያቀርቡት የመረጃ ጥያቄ አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት ረገድ፤ የማኅበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርሞች እና ሌሎች የበይነ-መረብ አገልግሎት ሰጪዎች በፕላትፎርሞቻቸው ለሚጠቀሙ ሕፃናት ደኅንነት ንቁ አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሕጎችን እና ፖሊሲዎችን ማውጣት፤
- በ‹ሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን› ውስጥ ያለውን ‹የሕፃናት ሽያጭ፣ የሕፃናት የወሲብ ንግድ፣ እና የሕፃናት የብልግና ምስል-ወድምጽ [ፖርኖግራፊ] አማራጭ ፕሮቶኮል›ን ማጽደቅ፤
- እ.ኤ.አ. በ2014 የአፍሪካ ኅብረት ያወጣውን ‹የሳይበር ደኅንነት እና የግላዊ መረጃ ጥበቃ› ኮንቬንሽንን (Convention on Cyber Security and Personal Data Protection) መቀበል፤
- የሕግ ማሻሻያዎች ሲደረጉ፤  የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን በመቅረፍ ረገድ ምርጥ አቅጣጫዎችን ከሚሰጡ ከዓለም-አቀፍ ኮንቬንሽኖች ጋር ለማጣጣም መሞከር፤ ለምሳሌ ያህል በአውሮፓ ምክር ቤት የወጡት ‹ሕፃናትን ከወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ለመጠበቅ የወጣ ኮንቬንሽን› (የ‹ላንዞሬት ኮንቬንሽን›)፤ እና ‹የሳይበር ወንጀል ኮንቬንሽን› (የ‹ቡዳፔስት ኮንቬንሽን›) ይጠቀሳሉ፡፡

## ማስተማር

- በበይነ-መረብ የሚፈጸሙ የወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነገረ-ጉዳዮችላይ ክስ ለመመሥረት ስለሚያስችሉ የሕግ ድንጋጌዎች ላይ ያተኮረ ሥልጠናን፤ በተለይም በቀበሌ እና በወረዳ እርከኖች ላይ ላሉት የፖሊስ አባላት እና ዐቃቤ-ሕጎች እንዲሰጥ ማድረግ፤
- የወሲብ ይሁንታ፣ የግል ድንበሮች፤ ወሲባዊ ምስሎችን በመቅረጽ፣ በመላክ፣ እና በመቀበል ሂደት ላይ ያሉ ስጋቶች እና ኃላፊነቶች ምንነትን የሚመለከቱትን ጨምሮ፤ ለሕፃናት ዕድሜ የተገባ እና ባህልን ያገናዘበ የሥነ-ጾታ ትምህርት በመላ ሃገሪቱ ላሉ ሕፃናት የተዳረሰ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ከትምህርት ቤቶች በተጨማሪ ያሉ ሁሉንም ዓይነት አውታሮችን መጠቀም፡፡ ይህ ዓይነቱ ዕውቀት በበይነ-መረብ ላይም ሆነ በአካል/በፊትለፊት መደረግ የሌለባቸውን አደገኛ ወይም ያልተገቡ ግንኙነቶችን ሕፃናት ለይተው እንዲያውቁ ያግዛቸዋል፡፡
- ስለ የሕፃናቱ የበይነ-መረብ እንቅስቃሴ ወይም ውሎ የተንከባካቢዎችን ግንዛቤ ማሳደግ፤ ይህም የበይነ-መረብ መገልገያዎች ያዘሉትን አደጋዎች ብቻ ሳይሆን ጠቀሜታዎቹንም ጭምር ለተንከባካቢዎች በሚያሳውቁ፤ እንዲሁም የሕፃናቱ የበይነ-መረብ አጠቃቀም ላይ እንዴት አብረው እንደሚሳተፉ እና እንደሚያግዙ፤ ብሎም ሕፃናት በበይነ-መረብ ላይ አደጋ ወይም ጉዳት ሲያጋጥማቸው ይበልጥ ግልጽ የሆነ ውይይት ማድረግ ስለሚችሉበት አግባብ በሚያስተምሩ በማኅበረሰብ-ተኮር የግንዛቤ እና የትምህርት ፕሮግራሞች አማካኝነት ነው፡፡
- የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነክ ክሥተቶችን ለመጠቆም የሚቻልባቸው የአደጋ ማሳወቂያ መስመሮች (hotlines) እና የዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች (helplines) ያሉ መሆኑን እና እነዚህም አስቸጋሪ ገጠመኞችን በማሳወቅ ከቤተሰብ ወይም ከማኅበረሰቡ ውጪ ዕርዳታ የሚገኝባቸው አሠራሮች መሆናቸውን ምልአተ-ሕዝቡን የሚያስገነዝቡ ቅስቀሳዎችን ማካሄድ፤

## ውኅሎተ-ንዋይ

- የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደልን በመቅረፍ  ላይ የተሠማሩትን ሁሉም መሥሪያ ቤቶች በበቂ ገንዘብ መደገፍ፤ እንዲሁም ከ‹የጠፉ እና ለብዝበዛ የተጋለጡ ሕፃናት ብሔራዊ ማእከል (ጠ/ብ/የ/ሕ/ብ/ማእከል/ NCMEC) የሚሰጡ የሳይበር ጥቆማዎችን ጨምሮ ዓለም-አቀፋዊ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ምሪቶች (referrals) በተገቢው የፖሊሳዊ የምርመራ እርከኖች ተገምግመው ማለፋቸውን የሚያረጋግጥ ብቁ አሠራር እንዲፈጠር አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፤ ይህም በሕፃናት ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ እንዲቻል ነው፡፡
- ‹የተጎጂዎች ፈንድ›ን ከማቋቋም ጋር የተያያዙትን መመሪያዎች ተፈጻሚ ማድረግ፤ እነዚህም ለሕፃናት እና ለተንከባካቢዎቻቸው ነጻ የሕግ ድጋፍን፤ ጊዜያዊ መጠለያን፣ የሥነ-ልቦና ድጋፍ አገልግሎቶችን፣ እና መጓጓዣን ያጠቃልላሉ፡፡
- በተለይም በወረዳ እና በቀበሌ እርከኖች ላይ ያሉትን የፖሊስ አባላትን፣ ዐቃቤ-ሕጎችን፣ ዳኞችን፣ ጠበቆችን፣ የችሎት ሠራተኞችን፣ የሕፃናት ጥበቃ እና የግንባር ቀደም ሠራተኞችን የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ላይ ያተኮረ ሥልጠናን ለመቅረጽ እና ለመስጠት የሚያሻውን ወጪ መመደብ፤
- በሕፃናት ጥበቃ ላይ ይበልጥ ያተኮሩ የሥራ ክፍሎችን ለማቋቋም እና  ለሕፃናት-ምቹ ድጋፎችን መስጠት በሚችሉ በሠለጠኑ ወንድ እና ሴት ሠራተኞች ለማደራጀት እንዲቻል ለፌደራል ፖሊስ ኃይሉ ገንዘብ መመደብ፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የትምህርት ቤቶች መምህራንን/ሠራተኞችን፣ የጤና ሠራተኞችን፣ እና ለሕፃናት አገልግሎት የሚሰጡ የዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮችን የሚከውኑ ድርጅቶችን ጨምሮ፤ የግንባር ቀደም ማኅበራዊ አገልግሎቶች ላይ የተሠማራውን የሰው ኃይል አቅም ማጎልበት፡፡ ይህም የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ነክ ጉዳዮችን ጨምሮ፤ ሪፖርቶችን ለመቀበል ብቻ ሳይሆን ለሕፃናት የሥነልቦና-ወማኅበራዊ (psychosocial) ድጋፍን ለመስጠት የሚስችል አቅም ሠራተኞቹ ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ፤ ብሎም የአገልግሎቱን ዘላቂነትም እውን ለማድረግ   ነው፡፡

Funded by End Violence Against Children

Implemented by ECPAT INTERPOL unicef Office of Research-Innocenti

DISRUPTING HARM

## ወሳኝ ቁምነገሮች

**ዲስረፕቲንግ ሀርም በኢትዮጵያ  ካካሄዳቸው የተለያዩ የምርምር ሥራዎች ውስጥ አራት ወሳኝ ቁምነገሮችን ለመለየት ተችሏል፡፡**

1. በባለፈው ዓመት ብቻ፤ በኢትዮጵያ ከ12 እስከ 17 ዓመት ዕድሜ ካላቸው በይነ-መረብ ተጠቃሚዎች ውስጥ፤ 10 በመቶዎቹ ዓይነታቸው በከፋ የበይነ-መረብ ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ድርጊቶች ተጠቂ ሆነዋል፡፡ ይህም በመያዣ በማስገደድ (blackmailing) ሕፃናት በወሲባዊ ተግባራት እንዲሳተፉ ማድረግን፣ እነሱን የሚያሳዩ የገዛ ወሲባዊ ምስሎቻቸውን ያለ ይሁንታቸው ለሌሎች ማጋራትን፣ በገንዘብ እና በስጦታ በመደለል በወሲባዊ ተግባራት እንዲሳተፉ ጫና ማድረግን ይጨምራል፡፡ አኃዙ ከጠቅላላው የሕዝብ ብዛት አንጻር ሲሰላ፤ በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ 300 ሺህ የሚገመቱ ሕፃናት ከእነዚህ ጎጂ ድርጊቶች በአንዱ መጠቃታቸውን ያመለክታል፡፡
2. በኢትዮጵያ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ከደረሰባቸው ሕፃናት ውስጥ፤ እንደ ዕርዳታ መጠየቂያ መስመሮች ወይም እንደ ፖሊስ ያሉ መደበኛ የአቤቱታ/ሪፖርት ማድረጊያ አሠራሮችን የተጠቀሙት በጣም ጥቂቶቹ  ብቻ ነበሩ፡፡
3. በዲስረፕቲንግ ሀርም የጥናት ቡድን ግምገማ መሠረት፤ የበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ሊባል የሚችልን አንድም ነገረ-ጉዳይን የፍትሕ ሥርዓቱ እስካሁን ድረስ አስተናግዶ አያውቅም፡፡ ለበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል የተሻለ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል፤ የሕግ አስከባሪውን እና የዳኝነት ሥርዓቶችን ዕውቀት፣ አቅም፣ እና አደረጃጀት የሚያጎለብት ማርሽ ቀያሪ ውኅሎተ-ንዋይ ማድረግ ይደር የማይባል አስቸኳይ ጉዳይ ነው፡፡
4. ሥራን ለማሣለጥ እንዲቻል ከየበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል ጋር የተያያዙ አስፈላጊ የሆኑ የሕግ ማሻሻያዎችን ማድረግ ያሻል፡፡

**ሙሉው ሪፖርት እና ሁሉም የምክረ-ሐሳቦች ዝርዝር በ bit.ly/DH_reports ላይ ይገኛል፡፡**

## ዲስረፕቲንግ ሀርም

ኢትዮጵያን የሚመለከተው የዲስረፕቲንግ ሀርም-ኢትዮጵያ (Disrupting Harm – Ethiopia) ጥናት፤ 13 የምሥራቃዊ እና የደቡባዊ አፍሪካ ሃገራትን እና የደቡብ-ምሥራቃዊ የእስያ ሃገራትን በማቀፍ በበይነ-መረብ የሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ እና በደል  ላይ ካተኮረው ፋና-ወጊ እና በርካታ ሃገራትን ካካለለው የምርምር ፕሮጀክት ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ይህ ግዙፍ የምርምር ፕሮጀክት፤ የኢ/ሲ/ፒ/ኤ/ቲን (በእንግሊዝኛ ምሕፃረ ቃሉ ECPAT)፣ የኢንተርፖልን (INTERPOL)፣ የዩኒሴፍን (UNICEF)፣ እና በዓለም ዙሪያ ያሉ አጋሮቻቸው ያካበቱትን የምርምር አቅም ጥቅም ላይ ያዋለ ሥራ ነው፡፡ ለዲስረፕቲንግ ሀርም (Disrupting Harm) ድጋፍ ያደረገው በእንግሊዝኛ ስያሜው ‹ፈንድ ቱ ኢንድ ቫዮለንስ አጌይነስት ቺልድረን› (Fund to End Violence Against Children) የሚሰኘው ለጋሽ ሲሆን፤ ይህም ለጋሹ እየተገበረ በሚገኘው ‹ደኅንነቱ የተጠበቀ በይነ-መረብ› (Safe Online initiative) በሚሰኘው ውጥኑ አማካኝነት ነው፡፡

ከበርካታ ምንጮች የተሰበሰበውን ጥሬ መረጃ እርስ በእርስ በማመሳከር እና በሦስትዮሻዊ-ንጽጽር (triangulation) በማወዳደር ኢትዮጵያን የሚመለከተው ሃገር-አቀፍ ሪፖርት ተዘጋጅቷል፡፡ በጥሬ መረጃው መነሻነት የተቀመሩት ምክረ-ሐሳቦች፤ በመስከረም 2014 ዓ.ም. ላይ በአዲስ አበባ ተካሂዶ በነበረው የሃገር-አቀፍ የምክክር ጉባኤ ላይ ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

Funded by End Violence Against Children

Implemented by ECPAT INTERPOL unicef Office of Research-Innocenti